# "አካፋን  አካፋ" የማለት ፖለቲካዊ ባህልና የኢህአዴግ ተደራራቢ ድሎች

ከቢላል 05/27/13

እነሆ የደርግ አምባገነናዊ ስርዓት ግብዓተ መሬቱ የተፈፀመበትንና የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን ያሬጋገጡበትን  የድል በዓል 22ኛ ዓመት በማክበር ላይ እንገኛለን፡፡

ታዲያ ለዚህ ታሪካዊ ወር መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ትግል፣ ትግል ከሚሸቱት የድል አድራጊነት ወነቻችን ውስጥ አንዳንዶቹን እያነሳን፣ ለሀገራችን ወቅታዊ ጉዳይ በሚስማማ መልኩ ብንጨዋወት ምን ይለናል . . . !?

በዚህ አጭር ማስታወሻዬ ላወሳ የፈለኩት ቁም ነገር ኢህአዴግ እንደ ድርጅት ከሚታወቅባቸው የትግሉ እሴቶች መካከል አንዱ ስለሆነው ‹‹አካፋን አካፋ›› ብሎ የመጥራት ባህል ነውና አብረን እንቆይ፡፡

በቅድሚያ ግን ወደ አዲሲቱ ኢትዮጵያ ያደረሰንን የሞት ሽረት ትግል መርተው የግንቦት 20ውን ታሪካዊ ድል እንድንቀዳጅ በማድረግ ረገድም ሆነ፣ ላለፉት 22 ዓመታት ሀገራችን ውስጥ የተስተዋለውን ፈጣን ዕድገት ለማምጣት ያስቻለንን በሳል አመራር በማሳየት፣ የታላቅ ስብዕና ባለፀጋነታቸውን ያስመሰከሩት፣ ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ በአፀደ ስጋ የማይገኙበት በመሆኑ የዘንድሮውን የድል በዓል ከእስከዛሬው የተለየ እንደሚያደርገው ማስታወስ ተገቢ ይመስለኛል፡፡

ደግሞስ በኢህአዴግ የትግል ሒደት ዙሪያ የሚያተኩሩ ቁም ነገሮችን እያነሳን መጨዋወት ካለብን ከወዲዜናዊ (ከመለስ) አይረሴ ንግግሮች ውጭ ይቻላል እንዴ? እንደኔ እምነት ፈጽሞ የሚቻል አይደለም፡፡ እናደርገው እንኳን ብንል ጨዋታችን ለዛቢስ እንደሚሆን መገመት አይከብድም፡፡ ስለዚህም ለቀድሞው ጠ/ሚኒስትራችን ለክቡር አቶ መለስ ዜናዊና ለመላው የትግሉ ሰማዕታት ያለኝን ከልብ የመነጨ አክብሮት በዚህ አጋጣሚ እየገለጽኩ፣ አሁን በቀጥታ ላወጋችሁ ወደፈለኩት ጉዳይ ልውሰዳችሁ፡፡

ወቅቱ የዛሬ 28 ዓመት በ1977 ዓ.ም. ነው፡፡ 1977 ዓ.ም. ደግሞ ሰሜናዊው የሀገራችን ክፍል (በተለይም ትግራይ) የዝናብ እጥረት ባስከተለው እጅግ በጣም አሰቃቂ የድርቅ አደጋ የተጠቃበት ክፉ ዘመን እንደነበር ይታወሳል፡፡

እናም ያኔ ከደርግ መንግስት ጋር የትጥቅ ትግል በማካሔድ ላይ የነበረው ህወሐት፣ ድርቅ ባስከተለው የምግብ እጥረት ምክንያት የሚላስ የሚቀመስ አጥቶ በረሀብ አለንጋ እየተገረፈ እንደቅጠል መርገፍ የጀመረውን የክልሉን ህዝብ (በይበልጥ ደግሞ የደቡብ ትግራይ ነዋሪዎችን) ከዕልቂት ለመታደግ ሲል እሱ በሚቆጣጠረው ነፃ መሬት በኩል ወደጎረቤት ሀገር ሱዳን ሔደው የሚረዱበትን ሁኔታዎችን በማመቻቸት ችግሩን ለመቅረፍ ያደረገው ጥረት የሚዘነጋ አይደለም፡፡

በ1977ቱ የድርቅ አደጋ እጅግ አስከፊ ገፅታ ከተስተዋለባቸው የራያ አዘቦና የዕንደርታ አውራጃዎች ወደ ሱዳን ሔዶ ሕይወቱን ለማትረፍ ፈቃደኛ የሆነውን ህብረተሰብ ወደ ጎረቤት ሀገር የማጓጓዙን ስራ ደርግ ቢደርስበት፣ የጦር አውሮኘላኖቹን ልኮ የባሰ ጥፋት ማስከተሉ እንደማይቀር አበክሮ የተገነዘበው ህወሐት፣ በሺህ ኪሎ ሜትር የሚገመተው የህይወት አድን ጉዞ ለሊት፣ ለሊት ብቻ እንዲደረግ ውሳኔ ላይ ለመድረስ መገደዱም የሚረሳ ጉዳይ አይደለም፡፡

አብዛኛው የድርጅቱ ታጋይ ድርቅ አመጣሽ የተፈጥሮ አደጋና ወታደራዊው የደርግ መንግስት የሚያደርሰው መጠነ ሰፊ ጉዳትና አረመኔያዊ ጥቃት ተደማምረው ችግሩን ይበልጥ አወሳስበውት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ድርጅቱ እንደምንም እየተሹለከለከ የረሀብተኛ ወገኖቹን ህይወት የማዳን ተልዕኮ ለመፈፀም ከላይ ታች ማለቱን አላቋዋረጠም ነበር፡፡ በዚያ ቀውጢ ወቅት ነው እንግዲህ የህወሐትን አመራር በሁለት ጐራ ክፍሎ ለቀናት ሲያከራክር የሰነበተውና ‹‹አካፋን አካፋ ነው›› የማለት የግምገማ ስርአት በጉባኤው ተመክሮ - ተዘክሮበት፣ በመጨረሻም ህዝባዊ ትግሉ የድል ባለቤት ይሆን ዘንድ ስርአቱ ባህል ሆኖ እንዲቀጥል የተወሰነው፡፡

‹‹ምስረታ ማሌሊት›› በመባል የሚታወቀው ያ ታሪካዊ ጉባዔ፣ በትግራይ ማዕከላዊ ዞን ልዩ ስሙ ‹‹ወርኢ›› ተብሎ በሚጠራ ሸለቆ (ወንዝ) ውስጥ የተካሔደ ሲሆን፣ የሞት ሽረት ክርክሩን በፍጹም ዲሞክራሲያዊነት ያካሔዱት መሪ ተዋናይ ደግሞ ‹‹አካፋን አካፋ ነው ማለት ይኖርብናል›› የሚል መሰረተ ሃሳብ ይዞ ተነሳ፡፡ በተቃራኒው የለም ይህ መሆን የለበትም የሚል ወገን ተነሳ፡፡

በዛ ህወሐት የአስር ዓመታት የትጥቅ ትግል ጉዞውን በጥልቀት በገመገመበት ታሪካዊ ጉባኤ ላይ፣ የሁለቱንም ወገን አቋም የያዘውን ሃሳብ ለጉባኤተኛው አቅርቦ በድርጅቱ ታሪክ ጉልህ ስፍራ

የሚሰጠውን ‹‹አካፋን አካፋ ማለት ይኖርብናል›› የሚል መከራከሪያ የነበረው የእነ መለስ (ወዲ ዜናዊ) በሰፊ የድምጽ ብልጫ ለማሸነፍ ቻለ፡፡

አሸንፎ የወጣው የድርጅቱ አመራር በወቅቱ ያራመደው ሃሳብ ‹‹ህወሐት ያነገበው ዓላማ የሀገራችንን ህዝቦች የዘመናት ጥያቄ የሚመልስ መሆኑ ባያከራክርም፣ ደርግን አስወግደን ይህን ህዝባዊ ዓላማችንን ወደ መላው ኢትዮጵያ ለማድረስ እንችል ዘንድ ግን የትጥቅ ትግሉ ከተራ የደፈጣ ውጊያ ባለፈ መልኩ ተከታታይ የማጥቃት እርምጃ ለመውሰድ ወደሚያስችለን ምዕራፍ መሸጋገር ይጠበቅበታል›› የሚል ሲሆን ፣ ለዚህ መከራከሪያቸውና ዋነኛ የማሳመኛ ነጥብ አድርገው ያቀረቡትም፣ ከዚያ በፊት በነበረው የአስር አመታት ጉዞ ትግራይ ውስጥ የሚገኙ ጥቂት ወረዳዎችን ብቻ፣ ከመቆጣጠር ባልዘለለ ሁኔታ ተወስነው መቆየታቸውን ነው፡፡

በዲሞክራሲያዊ የክርክር ሒደቱ የጉባኤተኛውን ድጋፍ አግኝቶ ያለፈውን የለውጥ አመለካከት፣ አምርረው የሚቃወሙት ጥቂት የአመራር አካላት ከድርጅቱ ጋር መቀጠል እንደማይፈልጉ (ወደ ሱዳን አገር መሰደድ እንደሚመርጡ) አሳወቁ፡፡ በዚህ ወቅት ነበር አንድ እንደ አብዛኛው ታጋይ ሁሉ፣ ፀጉሩን ያንጨበረረ፣ ጺሙን ያጐፈረ ጠይም ቀፍጣና ወጣት፣ ከወደ መድረኩ ‹‹እንደዚህ ዓይነት ሰው ሲያጋጥም በአማርኛ ምንድነው የሚባለው?›› የሚል ጥያቄውን በትግርኛ ቋንቋ ለጉባኤተኛው ሲያቀርብ ተደመጠ፡፡

የዋሻ ውስጡን አዳራሽ ካጨናነቁት ወንድና ሴት የትግል ጓዶቹ መካከል ፈጠን ብሎ ጥያቄውን የሚመልስለት ሲያጣ ጊዜም ‹‹መንገዱን ጨርቅ ያርግልህ ነው የሚባለው በአማርኛ እሺ!›› ሲል ራሱ እቅጩን ለመናገር ተገደደ፣ መድረኩ ላይ የነበረው ቀፍጣና ወጣት ታጋይ፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) ዛሬም ድረስ የሚታወቅበትን ‹‹አካፋን አካፋ›› የማለት ፖለቲካዊ ባህል፣ በ1977ቱ የማሌሊት መስራች ጉባኤ ላይ "ሀ" ብሎ የጀመረው ያ ፀጉሩንና ጺሙን ያጎፈረ በረሽኛ ወጣት የትግል ሰው፣ ላለፉት 21 ዓመታት ይህችን ሀገር የመምራትን ታሪካዊ ሃላፊነት ተሸክሞ የቀየውና የሰለጠነውን ዓለም ጭምር ያስገረመ ብቃት ያሳየው፣ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትራችን ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ አስረስ መሆኑን ልብ በሉልኝ፡፡

ከ1967 ዓ.ም. እስከ 1977 ዓ.ም. ባሉት ድፍን አስር ዓመታት ውስጥ የነበረው ዘገምተኛ የትጥቅ ትግሉ ጉዞ እሱ አርቆ ለሚያልመው የአዲሲቱ ኢትዮጵያ ምስረታ ዕውን መሆን የማይመጥን እየሆነበት በቁጭት ሲብሰለሰል ይስተዋል የነበረው ብላቴናው ታጋይ መለስ፣ አሁን እነዚያን

የህይወት ዘመን ውብ ህልሞቹን ለማሳካት ይቻል ዘንድ መሪ ድርጅቱ ህወሐት ምን ማድረግ እንደሚጠበቅበት በሚገባ ተረድቷል፡፡

የመጀመያው ቁልፍ ጉዳይ የነበረውም፣ በዚያ ጉባዔ የተሳተፉት የድርጅቱ አባላት መክረውና ዘክረው የተስማሙበትን ሃሳብ፣ ለእያንዳንዱ ታጋይ እንዲዳረስ የማድረግ ስራ መስራትና እንደ ድርጅት ከአመራር አካላት እስከ ተራ አባላት ድረስ ደረጃ በደረጃ የሚተገበር አመለካከትን የማጥራት ውይይት ማካሔድ ሲሆን፣ ይህን በማድረግ ረገድም መለስ የላቀ ሚና መጫወቱ ደግሞ ሌላው ታሪካዊ እውነታ ነው፡፡

ምንም እንኳን ብስል አዕምሮው የሚያፈልቃቸውን ዕጹብ ድንቅ አስተሳሰቦች፣ ለመሪ ድርጅቱ ድል አድራጊነት በሚጠቅም መልኩ እየቀመረ ከማቅረብ የቦዘነበት የታሪክ አጋጣሚ ባይኖርም፣ ህወሐት የ16 ዓመት የትጥቅ ትግል ጉዞውን በገመገመበት የ1977ቱ ጉባኤው፣ የወሰናቸውን መሰረታዊ የመዋቅር ለውጥ (ሪፎርም) ትግበራ ውሳኔዎች የታለመላቸውን ግብ እንዲመቱ ለማድረግ ሲል ያሳየው ልዩ ጥረትና በጥረቱም ልክ ያስመዘገበው አመርቂ ውጤት የመለስን ታላቅ የፖለቲካ ስብዕና ከመቼውም ጊዜ በላይ አጉልቶ ያወጣ ስለመሆኑ፣ በርካታ ጉዋዶቹና ድርሳናት ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ፡፡

በተለይም "የበረታው ይሩጥ፣ ለመሮጥ የሚያስችል አቅም የሌለው ቢያንስ  ያዝግም፣ መሮጥም፣ ማዝገምም ያቃተውና እንደችካል አንድ ቦታ ላይ ፀንቶ መቆምን የመረጠ ሰው ደግሞ፣ እንቅፋት እንዳይሆንብን መንገዱን ይልቀቅ" የሚል ቁርጠኛ መልዕክት ያዘለውን የትግርኛ መፈክር በወቅቱ ለድርጅቱ የዕምርታ ንቅናቄ መሪ ሃሳብ ሆኖ እንዲያገለግል፣ በእያንዳንዱ ታጋይ አዕምሮ ውስጥ የማስረፅን ስራ ከማሳካት አኳያ የመለስ በሳል አመራር፣ የተጫወተው አወንታዊ ሚና በረዥሙ የኢህአዴግ ታሪክ ልዩ ስፍራ የሚሰጠው እንደሆነ ብዙዎቹ አንጋፋ አባላት ይስማሙበታል፡፡

በእርግጥም ትግራይ ውስጥ ተንሰራፍቶ የነበረውን ግዙፉን የደርግ መንግስት ሰራዊት፣ ሙሉ ለሙሉ ተጠራርጎ እንዲወጣ ማድረግ የተቻለው ‹‹ምስረታ ማሌሊት›› በመባል የሚታወቀው ልዩ ጉባኤ ከተካሔደ በኋላ በነበሩት ሶስት ዓመታት ውስጥ መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በወቅቱ መለስና ተከታዮቹ የፈጠሩት ድርጅታዊ መነቃቃት ያመጣው ያልተጠበቀና አስገራሚ እምርታ ስለመሆኑ የወቅቱ ታጋዮች ሁሉ የሚመሰክሩት  እውነታ ነው፡፡

‹‹አካፋን አካፋ›› በማለት መርህ ላይ የተመሰረተው የትጥቅ ትግሉ ባህል በፈጠረው መነቃቃት ምክንያት የመጣውን ለውጥ ይበልጥ አስገራሚ የሚያደርገው ሌላው ጎኑ በተከታዮቹ 3 ዓመታት

(ከ1980 - 1983) ውስጥ የኢህአዴግ ሰራዊት የደርግ ኢሰፓን አምባገናዊ አገዛዝ ሙሉ በሙሉ ገርስሶ የግንቦት 20ውን ታሪካዊ ድል ለመላው የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሊያበስር የመቻሉ ታሪካዊ ጉዳይ ነበር፡፡

አፈሩን ገለባ ያድርግለትና ታላቁ መሪያችን መለስ ዜናዊ አስረስ፣ ያኔ በትጥቅ ትግሉ ዘመን ኢህአዴግ በሰው በላው የደርግ ወታደራዊ አገዛዝ ላይ ተደራራቢ ድል እንዲቀዳጅ ያደረገውን የእምርታ ንቅናቄ ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ ይህችን ሀገር የመምራት ታሪካዊ ሃላፊነት የተሸከመው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር፣ የአስር አመት ጉዞውን በገመገመበትና ለኢትዮጵያ ሕዳሴ ፅኑ መሰረት የጣለበትን የፈጣን ልማት አቅጣጫ በቀየሰበት የ1993ቱ ድርጅታዊ የእምርታ ንቀናቄም፣ እንደተለመደው ሁሉ፣ የመሪ ተዋናይነት ሚናውን በብቃት ሲወጣ ማየታችን አይካድም፡፡

ከዚያን ወዲህ ባሉት 10 ያህል ተከታታይ ዓመታት አገራችን ያስመዘገበችው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት የ1993ቱ ድርጅታዊ የተሃድሶ ንቅናቄ ድምር ውጤት ያስገኘው እምርታ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ (ጉዳዩን የበለጠ ለመረዳት የአቶ በረከት ስምኦንን ‹‹የሁለት ምርጫዎች ወግ›› መመልከት ይችላል፡፡) በመሆኑም፣ ይህ ‹‹አካፋን አካፋ›› የማለት ፖለቲካዊ ቁርጠኝነትን የሚጠይቀውና መሰረቱ ኢህአዴግ የሆነው የትግል ባህል ተጠናክሮ የሚቀጥልበትን 3ኛ ዙር የእምርታ ንቅናቄ መጀመር ያለብን ይመስለኛል፡፡

እንደኔ እምነት ግን የበረታው በፈጣን ልማት ጎዳና ያለ አንዳች ማመንታት እንዲሮጥ፣ ለመሮጥ የማያስችል አሳማኝ ምክንያት የሚያቀርብ ካለ ደግሞ፣ ቢያንስ ቢያንስ አቅሙ የሚፈቅደውን ያህል ቅን ጥረቱን እንዲጀምርና እንዲሁም፣ የግንቦት ሃያው ታሪካዊ ድል ውጤት በሆነው የኢትዮጵያ ህዳሴ ጉዞ፣ “መሮጥም-ማዝገምም አይመለከተንም” ብለው ለደመደሙ የኩርፊያ ፖለቲከኞች ጭፍን ተቃውሞ፣ በጉዳይ አስፈፃሚነት የማያገለግለውን መሀል ሰፋሪ፣ ከኢህአዴግ ድርጅታዊ ሰልፍ ተመንጥሮ እንዲወጣ ለማድረግ፣ በተለይም ህዝብ የሰጣቸውን የመንግስት ስልጣን ተገን በማድረግ ይህችን ምስኪን ሀገር የሚጠቅሙ መስለው የሚያደሟትን ሙሰኛ ሹማምንት፣ ለህሊናቸው ታምነው ሃላፊነታቸውን ለመወጣት ከሚተጉት እውነተኛ ታጋዮች ለመለየት እንችል ዘንድ ‹‹አካፋን አካፋ›› የማለቱ ባህል ከመቼውም ጊዜ በላይ፣ አሁን ያስፈልገናል ባይነኝ፡፡ በተረፈ ሁላችንንም እንኳን ለ22ኛው ዓመት የግንቦት ሃያ በዓል በሰላም አደረሰን እላለሁ!!